# ጰራቅሊጦስን ለመገልበጥ ይታገላሉ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ nigatuasteraye@yahoo.com
ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

*ሌሎች የቀሲስ አስተርአየን ጦማሮች ለማንበብ የሚከተለውን ድኅረ-ገጽ ይመልከቱ፥*
***http://www.medhanialemeotcks.org/***

ግንቦት ፲፭ ቀን በፈረንጆች May 23 ቀን የምናከብረው ጰራቅሊጦስ የሚባለው አመታዊ በዐል ለጥንታዊትና ለዛሬይቱ ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምንጭ እንደሆነ፥ ለዚህች ጦማር መፍለቅም ዓቢይ ምክንያት ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን፥ "ትምጣ" እያልን ለምንመኛት በሰማይ ላለችው መለኮታዊት መንግሥት ምሳሌና ምልክት ብትሆንም፥ ፊደል ለመጻፍ ወረቀት ወይም ብራና፥ ጽላት ለመኖር መንበር እንደሚያስፈልግ፥ ይህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችን (*የኛነት ክምችትነታችን*) ኢትዮጵያ የተቀረጸችባት ጽላት፥ ያረፈችባት መንበሯ ናት:: በመሆኗም ስለ ጰራቅሊጦስ አጭር መግቢያ ከሰጠሁ በኋላ: ስለ ኢትዮጵያ ምድራችን ትንሽ ተናግሬ ስለጥንታዊቷና የዛሬይቷ ቤተ ክርስቲያናችን (*ክምችትነታችንን*) በመዳሰስ ጦማሬን እደመድማለሁ::

## ጰራቅሊጦስ

በዓል ፶ን በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ቃልኪዳን ይዘው በዓለም ዙሪያ የተበተኑትን ሁሉ በየመአቱ ከተበተኑበት በኢየሩሳሌም እየተሰበሰቡ እንዲያከብሩት ራሱ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት አዘዘ (ዘዳ ፲፪:፳):: በዚህ እምነትና ትምህርት ውስጥ ያሉ ሁሉ በትእዛዙ መሠረት በየአመቱ ከያሉበት እየተሰበሰቡ ማክበር ቀጠሉ:: ይህ በዓል በ፴፫ ዐመተ ምሕረት ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሳ በ፶ኛው ቀን: ባረገ ባ፲ኛ ቀን ላይ ዋለ:: እንደተለመደው ለበዓሉ ሲሉ ከየቦታው የተሰበሰሰቡትን ሰዎች አምላክ ከሐዋርት ጋራ አገናኝቶ ቤተ ክርስቲያንን በሁሉም ሕሊና ውስጥ ቀርጾ ወደየመጡበት አገር ይዘዋት እንዲሄዱ ዕቅድ ነበረውና ይህን ባሕላዊና ኦሪታዊ በዓል ተጠቀመ::

አምላክ ባንድ በኩል በዚህ በዓል ምክንያት ሕዝቡን ከያሉበት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጡ አደርገ:: በሌላ በኩል ደግሞ "ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ"(ሉቃ ፳፬:፵፱) ብሎ ሐዋርያትን የትም እንዳይቀሳቀሱ አደረጋቸው:: ከዓለም ዙሪያ ለበዓሉ የተሰበሰቡት ሰዎች ክትት ብለው ሲገቡ፥ አስደናቂ ህብር ያለው እሳት ሐዋርያት በተሰበሰቡበት ቤት ላይ ቦግ ብሎ ታየ:: ከላይ እንደገለጽኩት በዚህ ባህላዊው በዓል የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከተለያዩ አገሮች ተሰብስበው የነበሩት ሰወች: አገር አቋርጠው የሄዱበትን ዓላማ ጥለው እሳቱ ወደተነሳበት ሐዋርያት ወደነበሩበት ቤት እንየሮጡ ሄዱ:: ይህ እሳት ሁሉን የሳበ ማግኔት ነበር:: ይህ እሳት ለሐዋርያት ድፍረት፥ ጀግንነት: እውቀትና ዕውነት ያስታጠቀ ኃይል ነበር:: በባህሉ ለተሰበሰሰቡት ግን የነበሩበትንና የሄዱበትን ጊዜያዊ ተልዕኮ የሚያስጥል ባሕልና ቋንቋ ሳያግደው ስሜትን፥ እምነትንና ግንዛቤን ስቦ የሚለውጥ ማግኔት ነበር::

ይህ ጰራቅሊጦስ የሚባለው ሁሉንም ስቦ ያገናኝ (divine magnetic power) ኃይል፥

ክርስቶስ እንደገለጸው: ራሱ ክርስቶስ ያስተማረውን ለማሳሰብ፥ ለማጽናናት፥ ለማስተማር፥ ለምስክርነት ለማዘጋጀት፥ የሰውን ረቂቅ ሕሊና እያበጠረ ወደ እውነት ለመምራት፥ ስለ ጽድቅ መጉደልና ስለ ፍርድ መዛባት: ሰባዊ ሕሊናን ለመወቅስ: ወደሰው የመጣ የረቀቀ መለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (ዮሐ ፲፬:፳፮-ምዕ ፲፮:፲፫):: ጰራቅሊጦስ ከክርስትና በፊት የኦሪቱ እምነት ተከታዮች የሚአከብሩትን ዓመታዊ በዓል ተጠቅሞ፥ ለዚህ ባሕላዊ በዓል የተሰበሰበውን ሕዝብ በገዛ ቋንቋው ነግሮ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ለመለወጥ፥ የሰው ልጅ ሊገልጸው በማይችለው እሳት መሳይ አካልነት ባለው ትንግርት ከተለያዩ አገሮች በመጡት ሰዎች ፊት በሐዋርያት ላይ ፈሰሰ (የሐዋ ፪:፩-፲፫)::

ማግኔት የማይንቀሳቀሰውን ወፈጥ ድንጋይ፥ እሳት አመድ የሚአደርገውን ግንድና ጭራሮ፥ ነፋስ የሚገፋውን ገለባ ቅጠልና አባራ፥ እንደማይስብ ሁሉ፥ የድንጋይነት መንፈስ ያለው፥ የተረትና የፍሬ አልባ ወሬ ምንጭ የሆኑ፥ ባሉባልታና በሐሜት የሚገፋ ገለባ ባሕርይ ያለውቸው ጰራቅሊጦስ ያልሳባቸው ሰዎች ተቀላቅለው ገብተው ነበር::

## ሰዎች የመጡበት አገሮች

ከላይ እንዳልኩት፥ ፊደል ለመጻፍ ወረቀት ወይም ብራና፥ ጽላት ለመኖር ደግሞ መንበር እንደሚያስፈልግ ለዚህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን (ክምችነታችን) ኢትዮጵያ መንበሯ ወይም የተቀረጸችባት ጽላቷ ናትና፥ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን (ክምችትነታችን) ከመሻገራችን በፊት ስለ አገራችን ኢትዮጵያ ከተጻፉት የታሪክ መዝገቦች ሁለት አንቀጾች ልጥቀስ፥

ቅዱስ ሉቃስ እንደመዘገበው ለዚህ በዓል የተሰበሰቡ ሰዎች የጳርቴና፥ የሜድ፥ የኢላሜጥ፥ የቀጳዶቅያ፥ የጳንጦስ፥ የፍርግያ፥ የጵንፍልያ፥ የግብጽ፥ የቀሬና፥ የሊቢያ ሰዎች ነበሩ:: የተጠቀሱት ቦታዎች ከሮም በቀር በሰፊው አድማሳቸው በሚታወቁት አገሮች ውስጥ የነበሩ ወረዳወችና አውራጃዎች ነበሩ (የሐዋ ፪:፱-፲፩):: ቅዱስ ሉቃስ በዚህ አንቀጽ ላይ ሰፊዋን ኢትዮጵያን ባይጠቅስም: በሌላ አንቀጹ ቅዱስ ፊልጶስ በጋዛ ወንዝ ያጠመቀውን ጃንደረባ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ መጠቆሙን ሳንረሳ፥ በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ ለምን ኢትዮጵያን እንደዘለላት ለመረዳት ሌሎችን የታሪክ መዛግብት መመርመር ይጥቅማል:: ይህም ስለ መልክአምድራችን ብቻ ሳይሆን የዛሬይቱን ቤተ ክርስቲያናችንን ያለችበትን ሁኔታ በግልጽ ለመረዳትም ይረዳል::

ለምሳሌ:- Runoko Rashidi የተባሉ የታሪክ ሊቅ "Meluhha's precise geographical location has frequently been attached by modern scholars to ether the African Ethiopia, or the Indus valley (Harappan ) region of Pakistan and western India. Both regions were lands of black men, but Harppan, whose civilization was larger in area than ancient Mesopotamia and Egypt combined, was much closer to Sumer than African Ethiopia" (African Presence in Early Asia, Page 165). ብለዋል:: ማለትም:- Meluhha እና የPakistan አካል የነበረው Harappan ይባል የነበረው ምዕራብ ሕንድን ከፓኪስታን ጋር የሚአዋስነው ሸለቆ አፍሪካዊት ኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንደበረ የዘመኑ ጠበብቶች ይናገራሉ:: እነዚህ አገሮች የጥቁር አገሮች ሲሆኑ Harappan ይባል የነበረው በስልጣኔ የቅርብ ግንኙነት ከነበራቸው ከመስፖታምያና ከግብጽ ይልቅ የሰፋ ነበር:: ከአፍሪካዊት ኢትዮጵያ ይልቅ Sumer ለምትባለው ቦታም በጣም ቅርብ ነበር::

እኒህ ሊቅ፥ አፍሪካዊነት ቅጽሏን ሳትለቅ እንደመግቢያና መደምደሚያ አድርገው በዚህች አጭር አንቀጽ ኢትዮጵያን አቅርበዋታል:: በዚህች ቀን ቤተ ክርስቲያን በመሬት ኢየሩሳሌም ላይ ስትመሠረት: በሥልጣኔና በስፋት ከሚዋሰኑት ከነዚህ አገሮች ውስጥ ወረዳወችና አውራጃዎች የመጡ ሰዎች ነበሩ:: ሰዎች የመጡባቸው ወረዳዎች እንጅ እጅግ በጣም ርቀው ከመጡበት ከሮም በቀር የቀሩት ቦታዋች ከላይ በተጠቀሱት ድንበር ከሚያዋስናቸው ታላላቅ አገሮች ሥር የነበሩ ትንንሽ ከተማዎች ናቸው::

ታሪክ መዝጋቢው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፪ ላይ የጠቀሳቸው ብዙወቹ ወረዳዎችና አውራጃወች እንጅ በንድንበር የሚዋሰኑትን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሰፋፊ አገሮችን በሩቅ ካለችው ከሮም በቀር አልጠቀሳቸውም:: በዚህ ምዕራፍ ታላቋ ኢትዮጵያ ባትጠቀስም በዚህ ታላቅ በዓል ላይ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም ማለት አይቻልም:: በተጨማሪም በምዕራፍ ፰ ላይ የተጠቀሰው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊ እደሆነና ከዚያም ወዲህ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ ወደ ኢየሩሳሌም የሚአደርጉት ጉዞ: ኢትዮጵያውያን በዚያ ቀን በበዓሉ ላይ አልነበሩም ከሚያሰኘው ሩቅ ግምት ይልቅ፥ ነበሩ ለሚለው አባባል የሚቀርብ ይሆናል::

ይህ አጭር ታሪካዊ አንቀጽ የሚያሳየው አገራችን ኢትዮጵያ ከተዘከሩት አገሮች አቻወቿ የተለየች ጉደኛ አገር መሆኗን ነው:: ልበ ጎደሎ መሪ ሲፈጠርባት እንደጨረቃ የምትጎድል፥ ልበ ሙሉ መሪ ሲፈጠርባት የምትሞላ አገር እንደሆነች ቅዱስ ሉቃስና ከታሪክ መዝጋቢው አባባል እንማራለን:: ስለዚህ በዚህች ጦማር ኢትዮጵያ ስል ዛሬ አቶ መለሰ ቆርጠው ቆራርጠው የሰጡንን ቀን የጎደለባትን ግማሽ ጨረቃ መሳይዋን ኢትዮጵያ ማለቴ አይደለም::

ስለ ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለመናገር ከተቀረጸችባት ጽላቷ፥ ካረፈችባት መንበሯ ለመነሳት እንጅ፥ የኢትዮጵያን ስፋትና ጥበት ለመናገር አይደለም:: ኢትዮጵያ ቀን ሲጎድልባት እንደ ምትጎድለው፥ ቀን ሲሞላላት እንደምትሞላው ጨረቃ ቅርጿንና መጠኗን የምትቀያይር መሆኗን በመገንዘብ፥ የታሪክ ተወቃሽነትን ለዘመናችን መሪዎች ለነ አቶ መለሰና አቡነ ጳውሎስ አሸክመን በቤተ ክርስቲያናችን (ክምችትነታችን) ላይ እናተኩር::

## ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን

ቅዱስ ጳውሎስ "ወሰብሰ ዘነፍስ ኢይኤድሞ ዘመንፈስ ቅዱስ እስመ እበደ ይመስሎ. . . .ንሕነሰ ሐሊናሁ ለክርስቶስ ብነ" (፩ኛ ቆሮ ፪:፲፬-፲፮) እንዳለው በዚህ ሕዝባዊ ክምችት ውስጥ አንዲት ልብ የነበራቸው ሐዋርያት እንደነበሩ ሁሉ "ተኩላት መሰጥ እለ ኢይምሕክዋ ለመርዔት" (የሐዋ ፳:፳፱) ማለትም፥ ራሱ ክርስቶስ "የገሐነም ልጆች" ያላቸውን ሰዎች መስለው የገቡ አፍራሾች፥ አሉባልተኞችም ነበሩ:: በሐዋርያትና በፈሰሰው መለኮታዊ ኃይል ላይ ቀሉዱ፥ አፌዙ፥ ከዚያም የባሰ እንዲያውም "ጉሽ የወይን ጠጅ ተጥተው ሰክረዋል" (የሐዋ ፪:፲፫) እያሉም ያልሆነና ያልተደረገ ሐሜትና ትችት እየፈጠሩ ይህን ሕዝባዊ ክምችትነት ለማፍረስ ጥረታቸውን እዚያው ላይ ቀጠሉ:: የጰራቅሊጦስን እሳትነት ሳይለብስና ሳይጎርስ በነበረበት ባንድ ወቅት፥ ጴጥሮስ ያልሆነ ነገር በመናገሩ፥ ጌታችን ኢየሱስ "የሰውን እንጅ የእዚአብሔርን አታስብና አንተ ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ" (ማቴ ፲፮:፳፫) ብሎት ነበር:: አሁን ግን ጴጥሮስ በላዩ ላይ የፈሰሰውን እሳታዊ ጰራቅሊጦስ ለብሶና ጎርሶ ያለ ዓላማ ከንቱ ሩጫ በመሮጥ ራሳቸው ስተው ሌላውን ለማሳት እዚያው ላይ ሐሜትና አሉባልታ ማሰራጨት የጀመሩትን ቅስማቸውን ሰበረ:: "በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በአመጸኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት" ብሎ ክርስቶስን ከሰቀሉት ጨካኞችና ከሐዲወች ጋራ ጨፍልቆ በማቅረብ በልበ ሙሉነት በተግሳጽ ገረፋቸው (የሐዋ ፪:፳፫-፳፬):: ጴጥሮስ ቀጠለና ግርግር በመፍጠርና ግርግር ፈጣሪዎችን በመከተል ራሳቸው ከእውነትና ከተከሰተው አምላካዊ ሥራ ጋራ ተጋጭተው፥ ሌላውን ለመበከል የሰይጣን ተላላኪ አሉባልተኞች ሆነው እንዳይቀሩ: "ይህ በዚህ ቦታ ዛሬ በፊታችሁ እየተካሄደ በዓይናችሁ የምታዩት የሚነገረውም በጆሮአችሁ የምትሰሙት. . . . ለእናንተና ለልጆቻችሁ ከሩቅ ለሚጠራቸው ሁሉ ነው" (፪:፴፱) እያለ ያለአንዳች ይሉኝታና ፍርሐት በመገሰጽ አጥብቆ አስገነዘባቸው::

ይሕች በመሬት ላይ ብቅ ያለች ቤተ ክርስቲያን (ሕዝባዊት ክምችት) ምድራዊውን ጥቅማ ጥቅም ተጸየፋ፥ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የፈሰሰውን ጰራቅሊጦስ ለብሳና ጎርሳ፥ ክርስቶስ ያስተማረውን እያሰበች የተሸበረውን እያጽናናች፥ የክርስቶስን ፈቃድና ትእዛዝ የምትመሰክር ናት:: የሰውን ረቂቅ ሕሊና እያበጠረች ወደ እውነት በመምራት፥ ስለ ጽድቅ መጉደልና ስለ ፍርድ መዛባት: ሰባዊ ሕሊናን እየወቀሰች፥ ያለፈውን ትውልድ ከሚመጣው ትውልድ እያገናኘች የምትቀጥል ክርስቶስ በምድር ላይ ያስቀመጣት የረቀቀች መለኮታዊ ኃይል ክምችት ናት::

ከዚህ መለኮታዊ እሳት መሰል ባሕርይ ተለኩሳ በኛንደረባው ወደ አገራችን የመጣቸው ጥንታዊት ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን (የኛነት ክምችትነታችን) የሰውነትን መንፈስ ብቻ ሳይሆን የተቀረጸችባትን ጽላቷን፥ ያረፈችባትን መንበሯን ምድረኢትዮጵያን ማለቴ ነው፥ በጨለማው አፍሪካ ምድር ብቸኛ እንደ ኮከብ የምታበራ "ኀሐ ጽባሕ" (የጧት ኮከብ) አድርጋት ኖራለች:: በውስጧ የነበሩት እንደነ አቡነ ጴጥሮስ የነበሩት መንፈሳውያን መሪወቿም ይህን እሳት የለበሱና የጎረሱ ከሥጋውያን መሪዎች በላይ የእምነት: የእውቀትና የሞራል ሰዎች እንደነበሩ ብዙ የውጭ ታዛቢዎች ደጋግመው እንዲህ እያሉ ገልጸውታል::

Richard Pankhurst የተባሉ ሊቅ በአጼ ሰርጸ ድንግል ዘመን የነበረውን ሁኔታዋን "He gave the chief scholar to guide him in matters of the faith, and priests and deacons to conduct church services"( The Ethiopain Borderlands, Page 255) በማለት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ከሥጋውያን መሪዎች በላይ እንደነበሩ ገልጸዋል:: Marilyn Heldman የተባሉት ሊቅም "As more meaningful interaction developed between these officials and the local people. The people were encouraged to join in the services of the church and follow its teachings and practices, where the clergy were men of learning, they often entered into debate with local leaders on the relative merits of thier respective beliefs."(African Zion, Page 37) ብለዋል:: ካህናቱ የዕውቀት ሰዎች ስለነበሩ በመቀደስ፥ በመዘመርና ሃይማኖትን በመስበክ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ እራሳቸውን ሳይደብቁ በጥቅም ሳይደለሉ ይከራከሩ ነበር ብለዋል::

እነዚህ የውጭ ሊቃውንት ምስክሮች ይህን ሲጽፉ ፈጥረው አልነበረም:: ዮሐንስ አፈወርቅ "ይስሕበነ ጸዳሉ ለጸሐየ ጽድቅ" እንዳለው፥ እነዚህ ጸሐፊዎች ከማይጠፋው መለኮታዊ ብርሃን ተለኩሳ ወደ ኢትዮጵያ የመጣች ቤተ ክርስቲያናችን "ጸሐየ ጽድቅ ክርስቶስ" የተባለውን የክርስቶስን ፈቃድ የምታንጸባርቅ እንደነበረች በሚገባ የተረዱ ይመስላሉ:: ብርሃኑን የሚአንጸባርቅባት የክርስቶስ ጨረቃ ናት ሲሉ መጀመሪያ የአቡንነትን ተልዕኮ ይዞ ምድራቸውን የረገጠውን አባ ሰላማን የጥንት ኢትዮጵያውያን "ከሳቴ ብርሃን" ያሉበትን ምክንያት መሠረት በማድረግ ይመስላል::

ቤተ ክርስቲያናችን (ክምችትነታችን) ባንጸባራቂነት ባሕርይዋ ወይም ከሳቴ ብርሃንነቷ "አድኅን እግዚኦ ዛተኒ ሀገረ: ወካልዕታኒ አህጉረ ወበሓውርተ እለ በሃይማኖተ ዚአከ የኀድሩ ውስቴቶን" (ሊጦን ዘሰግህ) ማለትም: በቋንቋ: በባሕል በርቀት ተለያይተው የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ በአምሳሉ በፈጠራቸው አምላክ አንድ ናቸውና፥ ይህችን አገር፥ አንተን በማመን የጸኑ ሰዎች የሚኖሩባቸውን ሌሎችንም አገሮች ሁሉ አድን" የሚለውን የሰው መሆንን ልዕልና እያስጨበጠች ስታጸድስና ስታቀስ፥ በሌላ በኩል ይህን የተቀደሰ አላማ ስተው ለጥቅማ ጥቅማቸው ክርስትንና ይጠቀሙ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ

> "ተሰየመ አሉ ቀሲስ፥
> በእንግሊዙ ጳጳስ፥
> እጆቹን ሰጠ ለጥቂሮቹ፥
> መስቀሉን ለ[illegible]ጮቹ"

እያለች ቅዱስ ጴጥሮስ በገረፈበት የተግሳጽ ጅራፍ ስትገርፋቸው ኖራለች::

## የዛሬይቱ ቤተ ክስቲያናችን

ጥንታዊት ቤተክርስቲያናችንም የተመሰረተችው ጸራቅሊጦስ በሳባቸው፥ ከተለየየ አካባቢ በመጡ፥ የተለያየ ቋቋቋ በሚናገሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ሲገናኙ በሚግባቡ፥ ራሳቸውን ከምድራዊ ዓለም ባገለሉ ቅዱሳን ሰዎች ነበር:: የዛሬይቱን ቤተ ክርስቲያናችንን እንመራለን የሚሉት ግን እንደ ጥንቱ እንደ መሠረቱ እንኳን በተለያዩ መልክዓ-ምድር ያሉትን ሰዎች ሊያሰባስቡ፥ እንኳንስ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩትን ሊያግባቡ፥ ባንድ መልክዓ-ምድር ያለነውን በቋንቋ በመልክ የማንለያየውን

በጎጥ በወንዝና በቋንቋ እየከፋፈሉ በማሰቃየት ላይ ይገኛሉ::

የዛሬይቱ ክምችትነታችን መሪወች እየካኑና እያጸጹ የሚልኳቸው፥ ነገረ መለኮቱን ያጠኑትን፥ ህዝባዊ ፍቅር ያላቸውን ሳይሆን ለስሜታቸው ለመንደርተኝነታቸው ለቡድናቸውና ለግል ዓላማቸው ግብ የሚአገለግሉትን ብቻ ነው:: ለነገረ መለኮቱ ለሰባዊ ዜግነቱ ላንድነቱ መቆም ይቅርና ተዛምዶ ተዋልዶ በመልክ በባሕል አንድ ሆኖ ባንዲት አገር የሚኖረውን ሕዝብ ማካፋፈል የሚአስችል ጴጥሮስ የገሰጸበትን ምክንያት የተሸከሙትን ሰዎች እያስተማሩ በቤተ ክርስቲያናችን (በኛነት ክምችትነታችን) ለቀቁብን::

ሐዋርያት በተሰበሰቡባት ቤት ውስጥ ጳራቅሊጦስ ቤተ ክርስቲያንን በመሠረተባት ቀን አሉባልተኞች፥ ፌዘኞች፥ ዓላማ ቢሶች በግርግር ገብተው፥ እራሳቸው እውነትን ስተው፥ ሌላውን ለማሳት በሐዋርያትና በፈሰሰው መለኮታዊ ኃይል ላይ የቀለዱ፥ ያፌዙም እንደነበሩ አይተናል:: ከዚያም የባሰ እንዲአውም "ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረዋል" (የሐዋ ፪:፲፫) እያሉ የሐሰትና የሽፍጥ ትችት እንዳሰራጩትም ተገንዝበናል:: በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያናችን እኒህን ሰዎች የመሰሉ ጳጳሳት ተባዙ:: እነርሱም መሰሎቻቸውን ለማባዛት እያዲያቆኑ: እያቀሰሱ: እያቆመሱ: በቤተ ክርስቲያን (በእኛነታችን) ላይ ማሰማራታቸውን ተያያዙት::

ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው ነገረ መለኮት የምታስተምረው ወንጌል ሞራልና ስለሕዝብም የምትሰጠው ምስክርነት እንዲቀጥል "ለእናንተና ለልጆቻችሁ ከሩቅ ለሚጠራቸው ሁሉ ነው"( ፪:፴፱) እያሉ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ማስተማር ሲገባቸው፥ ወጣቶችን ሁሉ ለመጥፎ ተግባር በመሳሪያነት የሚጠቀሙ፥ ሳይፈልጉ ደግሞ የሚጠቀሙበትን ራሱን ወጣቱን እየከሰሱ ለዓለማዊ ዳኛ በማቅረብ ክምችትነታችንን ከደጀ ሰላምነቷ ወደ ጭቅጭቅ መድረክነት በመለወጥ ለመበታተን ትግላቸውን የሚያጋግሉ ናቸው::

ነገረ መለኮቱን ሳይረዱ የገቡ በመሆናቸው፥ ቅዱስ ጳውሎስ "ወዐየኑ ለሊሆሙ ወኢያአምሩ ፍካሬሁ ዘለሊሆሙ ይነብቡ"(፪ኛ ቆሮ ፲:፲፪) እንዳለው፥ እኔ ብጹዕ አባ እገሌ ቅዱስ አባ እገሌ እባላለሁ! እያሉ እራሳቸውን በማሞካሸት፥ እርስ በርሳቸው በመሞካከሽ፥ ቤተ ክርስቲያኛችንን (ክምችትነታችንን) በቴዎዶስዮስ ዘመን እንደነበረችው ቤተ ክርስቲያን (ክምችት) ለማድረግ እየታገሉ ነው:: ቴዎዶስዮስ የተባለው ሊቅ በነበረባት ቤተ ክርስቲያን ካሉባልት ከውሸትና ከማስመሰል፥ ከጥቅም ማሳደድ በቀር እውነተኛውን የሃይማኖት ትምህርት ለይተው ያልተገነዘቡ ለሕዝብ ደንታ የሌላቸው ካህናት መሳይ አስመሳዮች በዙባት:: "እሉ እለ ይፈቅዱ ይኩኑ መምሕራነ እምከመ ያእምሩ ትምህርተ እሉ እለ ይሄልዩ ቅድመ ጠቢባን እሙንቱ እንዘ ውርቶሙ አብዳን እሉ እለ ይፈቅዱ ይኩኑ ኖሎተ እምቅድመ ያእምሩ .....(ሃይ አበው ፹፪:፴፭) እያለ ቴዎዶስዮስ ተናገረ:: ዛሬ ለቤተ ክርስቲያናችን (ለክምችትነታችን) ከባድ ፈተና የሆነው፥ በዚህ ዘመን ፓትርያርክ የሆኑት ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የሰገሰጓቸው ጳጳሳት ብቻ ሳይሆኑ፥ እነሱም ደግሞ በግላቸው እያመነኮሱና እያቀሰሱ እያዳቆኑ የሚያሰራጯቸው ለመጥቀም የሥጋ ዘመዶቻቸውን ናቸው:: ብዙዎቹ ለግሪን ካርድ ለገንዘብ የሕቡን ስሜት ባሉባልታና በነገረ ሐውክ እየቀሰቀሱ ከመከፋፈል በቀር በውስጣቸው የተቀመጠ የነገረ መለኮቱ ቁም ነገር ባለመኖሩ፥ ስለነገረ መለኮቱ ሲጠየቁ ሲኖዶሱ ይጠየቅ የሚሉ፥ ሲኖዶስ ሲያምን የሚአምኑ፥ ሲኖዶስ ሲክድ የሚክዱ ናቸው::

ከአብዮቱ በፊት የነበረው ሲኖዶስ እነ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን በመሳሰሉ ታላላቅ ሊቃውንት ምክር ይመራ ስለነበረ ለነገረ መለኮቱ ተገዥ ነበር:: እንደነ የኔታ ብርሃኑ የመሰሉ መምሕራን "ቀድስዎ ለእግዚአብሔር በኩሉ ልብክሙ ወድልዋኒክሙ ሀልው በኩሉ ጊዜ ከመ ታውሥእው ቃለ ለእለ ይሴአሉክሙ በእንተ ዛቲ ተስፋክሙ" (፩ኛ ጴጥ ፫:፲፭) የሚለውን አንድም እያሉ ሲያስተምሩ "በቆራጥነት በፍጹም ልብህ ሳታወላውል የተማርከውን: ያወከውን በተጠየክበት ቦታና ጊዜ ሁሉ ተናገር: መስክር" እያሉ ነበር እንጅ: ስለነገረ መለኮት ስትጠየቁ ሲኖዶሱን ልጠይቅ በሉ ብለው አያስተምሩም ነበር:: ምክንያቱም እንደዛሬው የከፋ ክህደት ካልመጣ በቀር ብዙዎቹ የሲኖዶሱ አባላት ከየ ሊቃውንቱ እግር ስር ያደጉ፥ አሰረ ምንኩስናውን ምናኔውን የተረዱ ነበሩና ለነገረ መለኮቱ ዘበኞች እንጅ እራሳቸው ከነገረ መለኮቱ ጋራ የሚጋጩ አልነበሩም:: የትኅትናቸው ረድዔት ይጠቅማል ተብለው

በትኅትናቸው ወደ ጵጵስናው የገቡ ቢኖሩም፥ እንደ ዛሬዎቹ ብፁዕ ነኝ፥ ጳጳስ ነኝ እያሉ የግል ንብረት የሚሰበስቡ የግል ቤት የሚገነቡ አልነበሩም:: አገልግሎታቸውን የፈጸሙት ካብነቱ ሊቃውንት ሳይርቁ እየተማሩ ነበር:: ዛሬ ግን ካቡነ ጳውሎስ ጀምሮ በጣም ከጢቂቶች በቀር ብዙዎቹ የሲኖዱሱ አባላት ሳይማሩ በግርግር የገቡ በመሆናቸው፥ የትኛው ሠርጎ የገባ የትኛው የኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት እንደሆነ ለይተው የሚአውቁ አይደሉም:: በጉባዔ የዋሉ ጥቂቶች ቢኖሩም የጉባዔው ትምህርት እንዲህ ይላል ከማለት ይልቅ የሲኖዶሱ ጓዶቼ ምን ይሉኛል በማለት ሳይማሩ ከከተማ እየተመለመሉ በገቡት ብዘዎቹ ቁጥጥር ስር ወደቁ!!

የብሉያቱና የሐዲቱ ማብራሪያ ለሆኑት ለሊቃውንቱ መጻሕፍት ትርጓሜ: መምህራን እንደ የኔታ ቢረሳው የነበሩት ሊቃውንት፥ ብንያም የተባለው የእስክንድርያው ሊቅ "ንኩን ድልዋነ ይእዜ አ አኀውየ ወፍቁራንየ ለጾም ወለመልእክተ እግዚአብሔር ወለኩሉ ምግባረ ሠናይ ዘምሉዕ ትሩፋተ ወፈድፋደሰ ለሃይማኖት እንተ ኢትጸንን ዘሥሉስ ቅዱስ"(ሃይ አው ምዕ ፹፱:፪) ሲል የተናገረውን "ቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮቱን በሚገባ ያልተረዳውን ሰው መምህር ብላ በመሰየም ወደ ሕዝብ መላክም የለባትም" ይሉና "በዚህ መንገድ ወደ ሕዝብ የሚላክ መምሕር አላዋቂነቱን ለመሰወር ሲል ብዙ ያልሆነ ነገር እየዘባረቀ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ይከታል:: ከሊቃውንቱ ይልቅ ለሕዝብ ስለሚቀርብ በቤተ ክርስቲያን ማለትም በጠቅላላው ሕዝብ ላይ ከውጭ መናፍቃን የበለጠ ከባድ ችግር ፈጣሪ ይሆናል" እያሉ ነበር:: እንዳሉትም ዛሬ በአቡነ ጳውሎስ የሚመራው ሲኖዶስ የተሰባሰቡ ብዙዎቹ የግል ንብረት በመሰብሰብ የበረቱ፥ ለግል ምቾታቸው ሕንጻ ለመሥራት የፈጠሩ መነኮሳትንና ጳጳሳትን የሚአበዙ በሕዝቡና በሊቃውንቱ ላይ ልዑላንና መሳፍንት ሆነው ቁጭ አሉ!!

ቅዱስ ጳውሎስ "ወኢንትሀከይ ገቢረ ሠናይ: እስመ በድሜሁ ነአርሮ:: አምጣነ ብነ እለተ ንግበር ሠና የ ለኩሉ ወፈድፋደሰ ለሰብአ ሃይማኖት"(ገላ ፮:፱):: ብሎ ለገላትያ ክርስቲያኖች (ክምችቶች) ያስተማረውን የሐዲስ መምህሬ አንድም ብለው ያስተማሩኝ፥ "ለወገን ለአገር ለሰው ሁሉ የሚጠቅመውን በጎ ነገር ለማድረግ ችላ አትበል:: ይልቁንም ለምታገለግለው አምላክህ ቀራቢ ለሆኑት አቅምህ ጊዜህ በፈቀደልህ ሁሉ ጉልበትና አንደበት ሁናቸው" እያሉ ነው:: ዛሬ ግን ድንበር በተቃወሰበት አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ሲንገላታ፥ በጨለንቆ ገደል ሲጣል፥ ባርሲ ከተማ፥ በወለጋ በጅማ ያሉ ሁሉ ክርስቲያኖች ሲጨፈጨፉ መናገር ፖለቲካ መግባት ስለሆነ ዝም በሉ ሲባሉ ዝም የሚሉ ካህናት በዙ:: ለእምነት ለታሪክ ለሕዝብ ከመጮህ ይልቅ ለሳንቲም ለሹመት ለንብረት የሚታገሉትን በማሳማራት፥ ክምችትነታችንን ለማፍረስና ለመበታተን ጥረት እየተደረገ ነው:: እንዲአውም መንግሥት: የቤተ ክርስቲያኒቱን የመናገር ቅስሟን ለመስበር ሲል፥ የጎሳ ስም በመጥቀስ የተለየ ጎሳ ክምችት ናት በማለት በድፍረት እስከ መናገር ደረሰ::

አቡነ ጳውሎስ የሚልኳቸው ሕዝብ እየተሰቃየ፥ እየታሰረ፥ ወጣቶች ከትምህርት ገበታቸው እየተባረሩ ነው ለምን ዝም ትላላችሁ ሲባሉ፥ እነ አቡነ ጳውሎስ ሲከኗቸው "ይህ መንግሥት የሚአደርገውን ሁሉ ስሕተት አትዩ የሕዝቡንም ጩኸት አትስሙ:: ይህን ካደረጋችሁ ፖለቲካ ገባችሁ:: ፖለቲካና ኤሌክትሪክ አንድ ነው" እያሉ የሚነግሯቸውን ይዘው "እኛ ምን አገባን ይህማ የመንግሥትና ያቡነ ጳውሎስ ሥራ ነው" ይላሉ:: በዚህ ሁሉ ደባቸው ቤተ ክርስቲያናችንን (እኛነታችንን) የማታናገር ዲዳ: የማትሰማ ደንቆሮ በማድረግ ከሷነቷ ለመለየት እየታገሉ ናቸው::

ከሁሉም የበለጠ የሚአስገርመው ነገር:- ሕዝቡ የሚአውቀው ድንበሩ ሲፈርስበት፥ አስተዳደሩ ሲበላሽበት፥ ሲታሰር ሲገደል ከሚአሰማው ጮኸት ጋራ መተባበር 'ፖለቲካ' መግባት ነውና አትግቡ አትስሙ አትዩ እትናገሩ እያሉ፥ በተቃራኒው ሕዝቡ ለይቶ ስለማያውቀው ስለነገረ መለኮቱ መቃወስ ሲጠየቁ ደግሞ አዙረው ሕዝቡን ተጠያቂና ተከሳሽ ለማድረግ "ሕዝቡ ይወስን" ይላሉ:: "ሕዝብ ከመቼ ወዲህ ነው የነገረ መለኮት ወሳኝ የሆነው? የሕዝብ ወሳኝነት በአገር: በድንበር በንብረት ባስተዳደር በጠቅላላ ፖለቲካን በሚመለከት ሁሉ ነገር እንጅ በነገረ መለኮት (ዶክትሪን) አይደለም:: በመላ ዓለም የለም፥ ይህ ከሆነ ጠቅላላ ሕጻናቶች ባልቴቶች ሽማግሌዎች ሁሉ የነገረ መለኮት ሊቃውንት መሆን አለባቸው ማለት ነው:: ይህ ለራበው ሕዝብ ባመረ ሞሰበ ወርቅ ውስጥ ድንጋይ ከቶ ማቅረብ ነውና ሕዝቡን በብዙ መንገድ "አትበድሉት" ሲባሉ፥ እውነቱን ብንናገር ሕዝቡ ይደበድበናል፥ ብለው ሕዝቡን ሐሰትና አሉባልታ እንጅ እውነት የማይፈልግ፥ ተደባዳቢ እብድ

አርገው ያቀርቡታል::

ደበኝነታችው በዚህ የሚቆም አይደለም:: በሶስትና በአራት አመታት ኮርሶች እየለበለቡ ወደ ህዝቡ በሚአሰራጯቸው ጮሌዎች አማካይነት፥ ሊቃውንቱን መናፍቃን ናቸው እያሉ በሕዝብ እንዲጠሉ፥ በሕዝቡና በሊቃውንቱ፥ በሊቃውንቱና በሊቃውንቱ መካከል ግንኙት እንዳይፈጠር ሕዝቡም ከነዛ እምነቱ ጋራ እንዲጋጭና ሊቃውንቱን እንዲያሳድድ እያደረጉ ናቸው:: በመሠረቱ ለነገረ መለኮቱ መዛባት ሕዝቡ ወሳኝ ከሆነ፥ የቀደሙ ሊቃውንት ከወላጆች ጉያ ወጥጦ፥ ከተወልድ መንደር ርቆ፥ ከውሻ ጋር ታግሎ፥ በዳፍንት በእከክ ተሰቃይቶ የመማርን ባሕል ለምን አወረሱን? ከፍተኛውን ያብነቱን ትርጓሜ ለመማርስ ቀለብ ተሰፍሮልን መምሕራን ተቀጥሮልን ቦታ ተለይቶልን ከመጻሕፍት ጋር በመታገል ለምን ብዙ ዘመን አጣፋን? በጆት የተመደበለት የሊቃውንት ጉባዔ መምሪያስ ለምን አስፈለገ? ከሊቃውንቱ ጉባዔ የሚመነጨውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ነገረ መለኮት ለመጠበቅስ ለምን ሲኖዶስ የተባለው ድርጅት አስፈለገ? ቤተ ክርስቲያናችን (ክምችትታችን) መልሱን ካቡ ጳውሎስ ትጠብቃለች!!

ከገዳም ወጥታችሁ ከጳጳስ ርቃችሁ በክምችትነታችን ውስጥ የምትኖሩ መነኮሳት ትርጉሙ ሳይገባችሁ የግል ክብራችሁን በሕዝብ ጭንቅላት ላይ ለመካብ ቆሞሳት ነን የምትሉ አቂሙ:: ለነገረ መለኮቱ ዘበኝነት: ለሕዝበ ክርስቲያኑ ደህንነት ለመቆም ሳትበቁ ጳጳሳት ነን የምትሉ፥ ቆቡን አጥልቃችሁ፥ ቀሚሱን ለሰባውና ለወፈረው ሰውነታችሁ መሸፈኛ አድርጋችሁ፥ መስቀሉን በትቢት ተነፍቶ በተገለበጠው ደረታችሁ አንጥልጥላችሁ በሰው ፊት ለመታየት የምታደርጉትን ጥረት አቁሙ!! ይህ ዘመናችን ዮሐንስ አፈወርቅ "ወንስጥጥ ልብሰ ጽልመት ዘየአውደነ ወይከልአነ ነጽሮ" እንዳለው: ማስተዋል እንዳንችል አቡነ ጳውሎስ በገንዘብና: በሹመት ሕሊናችንን የሸፈኑበትን መጋረጃ ቀደን ሕሊናችን ነጻ እናውጣው::

ምን ልባት እንዴት አርጌ መቅደድ እችላለሁ? ብሎ የሚል ጥያቄ ካለ፥ ዮሐንስ አፈወርቅ መንገዱን ሳይናገር እንቅደድ አላለም:: "እመቦ ዘይብል በምንት ይትከላዕ እምኔነ ዝንቱ ግልባቤ ጽልመት: ንብሎ ሶበ ይስሕበነ ጸዳሉ ለጸሐየ ጽድቅ" (ተግሣጽ ገጽ ፪፻፵፪) ብሎ የመቅደጃውን ዘዴ ነግሮናል:: ማለትም:- እንዴት ሊቀደድ ይችላል ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር፥ ክርስቶስ ለሐዋርያት የላካት የመሳብ ኃይል ያላት እሳት በሳበችን ጊዜ ነው እንለዋለን" ብሏል:: እኛም ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውን መፈጸም እንችል ዘንድ አቡነ ጳውሎስና መሰሎቻቸው ከሚፈጥሩት የመከፋፈያ አሉባልታ ወጥተን የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት አባቶች ያስቀምጡልንን አብረን እንማረው: እናጥናው!

ይህን ለማድረግ ፈቃደኞች ካልሆን፥ አቡ ጳውሎስ ለሰርትፍኬታቸው የኦርቶዶክሱን ገረ መለኮት ገልጸው የጻፉትን ክደው፥ በስህተት የገባውን የባዕድ ሐይማኖት ተቀብለውና አጽድቀው እርስ በርሳችን ማተራመሳቸውን ልናውቅባቸው አንችልም:: በሌላ በኩል ደግሞ ከአሐት አብያተ ክርስቲያናት ከ አቡ ሽዳ ጋራ በሃይማኖት አንድ ን እያሉ ግብጽ ድረስ በመሄድ ይፈራረማሉ:: በተቃራው ደግሞ ይህንን አንድት ለማፍረስ "የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥላሴን ክዳለች፥ ስታለች" እያሉ እየጻፉ ለሕዝብ የሚያሰራጩትን ኮከብ ቆጠሪዎችን ማስተናገድዎን ያቁሙ ማለት አንችልም::

በተረፈ በባሕላችን አነጋገር ይሕችን ጦማር አጠቃልላለሁ:: የጥንት ኢትዮጵያውያን እውነት ስትጠፋባቸው ተቆጥተው ይናገሩ ነበር:: ይህን ዓይነት የቁጣ አነጋገር "እገሌ እሳት ለብሶ: እሳት ጎርሶ እገሌን ተናገረው" ይሉ ነበር:: ይህ ያለ ዋቢ ዘሎ የገባ አነጋገር አልነበረም:: አቡነ ጴጥሮስ እኛቸው የገባውን ሰንሰለት ረስተው፥ የተነጣጠረባቸውን መትረየስ እንደገለባ ረግጠው፥ ጣሊያን እንዲናገሩ ያዘዛቸውን ገልብጠው፥ "እንኳን ሕዝቡ መሬቷ አትገዛልህ" ያሉት ይህን እሳት በመጉረሳቸውና በመልበሳቸው ነበር:: ዛሬ ግን ይህን የጰራቅሊጦስን እሳት ለበሰውና ጎርሰው ስለእምነቱ፥ ስለሕዝቡ እውነቱን ሊናገሩ ቀርቶ፥ ሕዝቡ እየተራበ የሚጎርሱት ጮማና ክትፎ ጉሮሯቸውን ዘጋው:: የሚለብሱት ጥቁር ገበርዲን ወደ መ'ገነዣ በፍታ ተለውጦ የማይነገሩ እሬሳ አደረጋቸው!!

በወደቀ ሬሳ ላይ እንደሚጣሉ አንስርት: በሕዝቡ ሬሳ ላይ ተቀምጠው፥ በገነዘብና በስልጣን የሚጣሉ ናቸው:: ጰራቅሊጦስ "ለእናንተና ለልጆቻችሁ ከሩቅ ለሚጠራቸው ሁሉ ነው"(የሐዋ ፪:፴፱) በማለት ለቤተ ክርስቲያናችንን (እኛነታችን) የሰጠንን አደራ የበሉ ከሐዲወች ናቸው:: ቤተ ክርስቲያናችንን (እኛነታችንን) ወደ ሚቀጥለው ትውልድ ለማሻገር፥ "እሱ ወደ እውነት ይመራችኋል" ብሎ ክርስቶስ የመሰከረለት፥ የሰውን ረቂቅ ሕሊና እያበጠረ ወደ እውነት የሚመራ፥ ስለ ጽድቅ መጉደልና ስለ ፍርድ መዛባት ሰባዊ ሕሊናን ለመውቀስ ወደሰው የመጣ፥ የረቀቀው መለኮታዊ ኃይል ጰራቅሊጦስ ከቤተ ክርስቲያናችን ራስ ላይ እንዲያስወግዳቸው ወይ ለመሳሪያናት እንዲለውጣቸው ወደ ገዳም እየገቡ እንዲመንኑና ተምረው እንዲወጡ በድፈረት እንንገራቸው!!

ለማጠቃለል ያህል ጰራቅሊጦስ የሚያመለክተን በመልከዓ ምድርም ሆነ በቓንቓ የማይገናኙ ሰዎች አንድ መሆንንና መግባባትን ነው:: በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በመንግስት ዙፋንና በቤተክርስያናችን መንበር ላይ የተቀመጡት በአንድ መልከዓ ምድር ያለ ሕዝብ እየከፋፈሉ አንድ ዓይነት ቓንቓ የሚናገረውን ሳይቀር እየሰነጣጠቁ የጰራቅሊጦስን ሓይል ሊገለብጡት ይታገላሉ:: ዳሩ ግን ክርስቶስ ለጴጥሮስ "የገሃነብ ደጆችም አይችሉዋትም" (ማቴ ምዕ፲፮፥ቁ. ፲፰) ባለው መሰረት ሐሳውያን የጰራቅሊጦስን ተዓምር ሊያደናቅፉት እንዳልቻሉት ሁሉ፥ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ሕዝብ ተዋሕዶ ሊንዱት አይችሉም::

በአገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚካሄደው ነገር እያሳዘናችሁ፥ በነ አቡነ ጳውሎስ ሰንሰለት ታስራችሁ ቀን እንደጎደለባት ጨረቃ በተሸራረፈችው ምድራችን ላይ ባለችው እኛታችን (በቤተ መቅደሱ) ውስጥ ቆማችሁ "ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ" እያላችሁ በእንባ በሐዘን ሌሊትና ቀን ወደ ፈጣሪያችን በመጮሕ ላይ ያላችሁ፥ ካህናት አባቶቼና ወንድሞቼ:- በሌላ ጦማር እስክንገናኝ ድረስ በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፲፱ ላይ በተመሠረተው በታሪካዊው መወድስ ቅኔየ ለጊዜው እሰናበታችኋለሁ::

ቤተ ክርስቲያን ልዕልት መራተ ሌዋዊ፥ ዘበዘባና ተነጽሐት: በኖኅተ አዝማድ ዘኖሙ፥
ኢክህለት ትቁም: በከመ ልማዳ ቀዲሙ፥
እስመ ወድቁ በላዕሌሃ፥ ወተዋነይዋ ብዙኃን ኩሎሙ፥
ሠራዊተ ሌጊዮን ኃጥአን: ወደቂቀ ማኒ ወፒዮስ: እለ በኑፋቄ ያስተቃስሙ፥

ለዓለም:-
ምእመናንሂ ዘከንሳስ እስራኤላውያን ቆሙ፥
ለነገረ ፍትሕ ይትቀሀው፥ በጥቡዕ ልቡናሆሙ፥
ወእምትዕይንቶሙ መጽኡ አዝማደ አሐቲ እሞሙ፥
ዘተመትረ ኩለንትሃ: እስመ ተፈነወ ኃቤሆሙ፥

የዝንድሮውን በዓለ ፲ በዚህ ሁኔታ እንድናስታውሰው ያደረገን አምላክ: ከርሞ በተሻለ ሁኔታ ለማክበር ያብቃን::